


# ለመነጠቅ መዘጋጀት!




የእግዚአብሔር ህዝብ ለጌታ መመለስ የግድ እንዲዘጋጅ፣ ትንቢታዊ መልዕክቶች ከአለም ሁሉ ዙሪያ ወደዚህ እየመጡ ናቸው።




በራእዮች፣ ትንቢቶች፣ ጉብኝቶች እና ምልክቶች፣ ኢየሱስ ጥቂት ሰዓት እንደቀረ ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን ለዓለም ሰጥቷል። ነገር ግን ጥቂቶች ብቻ እያዳመጡና እየተዘጋጁ ናቸው።




በመሆኑም፣ ጌታ ሲመጣ፣ ጥቂቶች ብቻ ዝግጁ ይሆናሉ፣




እና አብዛኛዎቹ ሰዎች፣ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ጭምር (እንኳ)፣ ይቀራሉ!




አንዳንድ ትንቢታዊ ራእዮች እንዳሳዩት ሁሉም አባላት እንኳ ይቀራሉ! አንድም አባል እንኳ አልተወሰደም! (ከሕፃናት በስተቀር።)




ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ቀርተው ሲያገኙት ግራ ይጋባሉ። ያ እነሱ ላይ እንደደረሰ ማመን አይፈልጉም።




ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች አባላቶቻቸውን ለመነጠቁ (the rapture) እያዘጋጁ አይደለም። የመነጠቅ ርዕስ፣ የመጨረሻ ጊዜያት እና መከራው፣ በስብከቶቻቸው አልፎ አልፎ ይሸፈናል። እና ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ ርዕሱ በጣም ጥቂት ነው የሚያውቁት። (ስለ መነጠቅ:- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደጻፈው 24:36-51) (1ኛ ተሰሎንቄ 4:15-17)




በዚህም ምክንያት፣ በፓስተሮች (በካህናት) እና በቤተክርስቲያን መሪዎች ላይ በቀሩት ክርስቲያኖች (ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ገነት ከመሄድ በቀሩት) ታላቅ ቁጣ ይሆናል።

አባላቶቻቸውን ስላላዘጋጁ እነሱ ይወቀሳሉ።




በብዙ ቤተ ክርስቲያኖች፣ የሚያጫውት ብዙ አዝናኝ ነበር፣ እና ብዙ ክርስቲያኖች እያከበሩ (እየተዝናኑ) ነበር፣





**እየተጸጸቱ (ንሰሃ እየገቡ)** መቆየት ሲገባቸው።

ስብከቱ ወደሚያሳዝን ጸጸት (ንሰሃ) እየመራቸው አይደለም።





ለመነጠቅ ቀላል አይደለም። ልክ እንደ ንግስት አስቴር ዝግጅት፣ እሷን ለሠርጉ ለማዘጋጀት ጥብቅ ትኩረት እና  ቆራጥነት ይወስዳል።




ለኢየሱስ ለመዘጋጀት፣ ለኢየሱስ ሙሉ በሙሉ መማረክ እና መታዘዝ ይወስዳል።




ራስን ለጌታ ለማዘጋጀት የየእለት ንሰሃ (ጸጸት) እና መንጻት ያስፈልጋል። በሕይወታችሁ መቀየር ያለበት ማንኛውም ነገር ካለ ጌታን በትጋት መጠየቅ አለባችሁ። ዝም ብላችሁ ዝግጁ እንደሆናችሁ አታስቡ፣ ግን ጸልዩና ፈልጋችሁ አውጡ!





በማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ **መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም**።

መስቀላችሁን አንስታችሁ ማለት ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር ማስማረክ ማለት ነው። እና የክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን ይህ አስፈላጊ ነው። (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደጻፈው 10:38)




መነጠቁ (the Rapture) ጌታን በመንፈስ እና በእውነት የሚያውቁትን፣ በባህል እና በፎርም ከሚያውቁት ይለያል። አስመሳዮች እነማን እንደሆኑ ሙሉ ዓለም ሊያውቅ ነው!





በማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 7፣ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ በዚያን ቀን ብዙዎች ፦ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ፦ ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።




ከመለከቱ ጥሪ በኋላ፣ ንስሃ ለመግባት በጣም የዘገየ ይሆናል! ብዙዎች በከንቱ ይሞክራሉ፣ እንዳዘኑ (ይቅርታ በማለት) እየተናገሩ፣ እና ኢየሱስ እነሱን እንዲወስዳቸው እየተማፀኑ።

ነገር ግን ያ ፍሬ አልባ ይሆናል! ኢየሱስ ደግሞ ደጋግሞ እንዲህ ብሏል፣ እርሱ (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) የተዘጋጁትን እና ቅዱስ ሆነው የሚኖሩትን ብቻ ወደ እርሱ መንግሥት ይወስዳቸዋል።

የመፀፀት (ንስሃ የመግቢያ) ሰዓት(ጊዜ) አሁን ነው! በኋላ አይደለም።




ያልተነጠቁት (ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ መንግሥተ ሰማያት ያልሄዱት) እነዛ ሰዎች በሚያሳዝን ሁኔታ በታላቁ መከራ ውስጥ ይሄዳሉ!




ስለ ታላቁ መከራ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ **"በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና።"** (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 24:21)





ታላቁ መከራ የስቃይ (የማሰቃየት) ጊዜ ይሆናል። ኢየሱስ እንዳለ፣ **በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፣ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ**። (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 24:9)





ያ ጊዜ የክህደቱ ጊዜ ይሆናል። ኢየሱስ እንዳለ፣ **ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች**። (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምሥራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደጻፈው 24:12)




ያ ጊዜ መንግሥት በመንግሥት ላይ የሚነሳበት የጦርነትና የታላቅ ጉዳት ጊዜ ይሆናል። (ማርቆስ 13:8)




ያ ጊዜ የእጥረት እና የፍላጎት ጊዜ ይሆናል። በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ውስጥ፣ የአንድ ሙሉ ቀን ስራ ደሞዝ፣ የአንድ ቀን ምግብ ብቻ ነው ለማግኘት የሚያስችለው ብሎ ይነግረናል። (የዮሐንስ ራእይ 6:6)




በታላቁ መከራ ውስጥ(ጊዜ)፣ ፈጣን የማሕበረሰብ ስብራት (ውድቀት) ትእዛዝ ይኖራል።




እና ታላቅ ግራ መጋባት በዓለም አቀፍ ደረጃ ይሰራጫል። ምክንያቱም ታስረው የነበሩ ብዙ ክፉ መናፍስት፣ መሬት ላይ ይፈታሉ። (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ዮሐንስ ያሳየው ራእይ 9:2)




እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ይሆናል። ታላቁ መከራ በሁሉም ዋጋ መወገድ አለበት (ወደ መከራው እንዳንገባ በሁሉም ዋጋ ከፍለን ከጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ገነት መሄድ አለብን)።





ስለዚህ እንዴት ነው አሁን የምንዘጋጀው? ለመዘጋጀት ምን ማድረግ አለብን?




ኢየሱስ ቆንጆ(ውብ)፣ ንፁህ፣ እና ቅዱስ ለሆነች ሙሽራ ተመልሶ እንደሚመጣ የግድ ማወቅ አለብን! የኤፌሶን መጽሐፍ እንደሚገልጸው፣ እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ያለ ነጠብጣብ(እድፈት) ወይም መሸብሸብ (የፊት መጨማደድ) ወይም ያለምንም ነቀፋ ያለች የምታበራ ደማቅ ቤተ ክርስቲያን እየፈለገ ነው። ቅዱስ እና ያለነቀፋ ያለ አንድ ሰው። (በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን 5:27)





ኢየሱስ ከዓለም ጋር ለተጋባች ለሴተኛ አዳሪ (ለዝሙተኛ) አይመጣም።
[ከዓለም ጋር ለተጋቡ በሀጢአት ላሉ ለወንዶችም ለሴቶችም ማለት ነው]




መንግሥተ ሰማያት በእርግጥ እውን ናት በሚለው፣ በቹ ቶማስ መጽሐፍ። ኢየሱስ **ንፁሃን** እና **ታዛዦች** ብቻ እንደሚወሰዱ ጠቅሷል (ተናግሯል)።




ንፁህ በመሆን፣ ያ ማለት ራስን ከሱሶች፣ ከዝሙት ከሀጢአት፣ እና ከሁሉም አይነት ዓለማዊ ጠንካራ ስሜቶች አርቆ ማቆየት (ማራቅ) ማለት ነው። (በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የያዕቆብ መልእክት 1:27)




እና ታዛዥ በመሆን፣ ያ ማለት የእግዚአብሔር ቃል የሚለንን እናደርጋለን ማለት ነው። ኢየሱስ እንዳለ፣ **ይህን ብታውቁ፣ ብታደርጉትም ብፁአን ናችሁ።** (የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሐዋርያው ዮሐንስ እንደጻፈው 13:17)





ለኢየሱስ ዝግጁ መሆን የሚፈልጉ፣ በሕይወታቸው ውስጥ ኢየሱስን የግድ መጀመሪያ ማድረግ አለባቸው። ሌላ ምንም ነገር ከኢየሱስ የበለጠ ፕራዮሪቲ (ቀደምትነት) ሊኖረው አይገባም።




We must remember what it says in Hebrews chapter 12. Without Holiness, no one will see the Lord.

በዕብራውያን ምዕራፍ 12 የሚለውን የግድ ማስታወስ አለብን። ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፣ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና። (ያለ ቅድስና፣ ማንም ጌታን የሚያይ የለም።)





በማቴዎስ ምዕራፍ 5 ከኢየሱስ የሚገኘው ይህ ቃል፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተደጋጋሚ አይጠቀስም። እንዲህ ይላል፣ **እላችኋለሁና ፦ ጽድቃችሁ ከፃፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።**

ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመታዘዝ በትንሹ እነሱ እያደረጉ ያሉትን ካላደረጋችሁ፣ እናንተ ዝግጁ አትሆኑም! (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 5:20)




ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ከባድ እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ አድርጎታል። (ማቴዎስ 19:23-24)




ከሴት ጓደኞችሁ ወይም ከወንድ ጓደኞችሁ ጋር እየተኛችሁ (ዝሙት እየፈጸማችሁ) ከሆነ፣

**እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!**




በድብቅ ፖርኖግራፊ (የወሲብ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮዎች፣ ኦውዲዎች፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ ልብሶች ወ.ዘ.ተ.) የምታዩ ከሆናችሁ፣

## እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!

(የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 5:28)




ዓለማዊ ወይም ለብ ያላችሁ ከሆናችሁ፣

# እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!


(ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ዮሐንስ ያሳየው ራእይ 3:16)




ጥላቻ (ቂም) ወይም ይቅርታ አለማድረግ በልባችሁ ይዛችሁ ከሆነ፣


**እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!**

(የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 6:15)




ወደ ተቀረፁ ምስሎች፣ ወይም ወደ ቅዱሳን እየጸለያችሁ ማንኛውንም አይነት ጣኦት አምልኮ እየፈጸማችሁ ከሆነ፣

**እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!**




የጌታን ቀን የማታከብሩ ከሆናችሁ እና የእርሱን ቀን ቅዱስ አድርጋችሁ የማትጠብቁ ከሆነ፣ የራሳችሁን ስራ ወይም በእርሱ ቀን ቢዝነሳችሁን የምታከናውኑ (የምታካሂዱ)፣

**እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!**




የሰነፎቹን ደናግል (ቆነጃጅት) ምሳሌ አስታውሱ፣ መቅረዛችሁ በዘይት የተሞላ እና በደማቁ እየበራ ያለ ካልሆነ፣

## እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!

(የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 25)




እንደተቀረው ዓለም እየኖራችሁ፣ ጨዋቸውን ያጡ ክርስቲያን ከሆናችሁ፣

**እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!**

(የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 5:13)




ሌላው ጠቃሚ ነገር ገንዘብ ነው። ለእርዳታ እና ወንጌልን ለማውጣት (ለማሰራጨት) ብር ያስፈልጋል።





ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች አሥራትና እርዳታ(ስጦታ፣ ስዕለት) ቸላ እያሉ ናቸው።





በውጤቱም በዓለም ዙሪያ ወንጌልን በፍፁም ሰምተው የማያውቁ ብዙ ሰዎች አሉ!

ምክንያቱም ሰዎች እና አስፈላጊ ሪሶርሶች እየተላኩ ስላልሆነ።

ያ ነፍሳትን እያስከፈለ ነው!




ደግሞ፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች ከገንዘባቸው እየሰጡ ስላልሆነ በዓለም ዙሪያ ብዙ ሰዎች እየሞቱ ያሉ አሉ።




የጌታን አሥራቶችና መሥዋዕቶች (ስጦታዎች) ከሰረቃችሁ…


**እናንተ ዝግጁ አትሆኑም!**

(ነብዩ ሚልክያስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተነበየው 3:8)




ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከጻፈው ከምዕራፍ 14 የታላቁን ግብዣ ምሳሌ ላይ እንመልከት።


በዚህ በኢየሱስ በተነገረው ምሳሌ፣ ሰዎች ለግብዣው ዝግጁ ያልነበሩበት ሶስት ምክንያቶች እንደነበሩ አይተናል።




ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ ፦ አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤ በእራትም ሰዓት የታደሙትን ፦ አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ እንዲላቸው ባሪያውን ላከ።


ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር። የፊተኛው ፦ መሬት ገዝቼአለሁ ወጥቼም ላየው በግድ ያስፈልገኛል ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው።

ሌላውም ፦ አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁ፤ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው። (ሉቃስ 14:16-19)





ሌላውም ፡- ሚስት አግብቼአለሁ ስለዚህም ልመጣ አልችልም አለው።

ባሪያውም ፡- ደርሶ ይህን ለጌታው ነገረው። በዚያን ጊዜ ባለቤቱ ተቆጥቶ ባሪያውን ፡- ወደ ከተማ ጎዳናና ወደ ስላች ፈጥነህ ውጣ ድሆችንና ጉድንሾችን አንካሶችንና ዕውሮችንም ወደዚህ አግባ አለው። (ሉቃስ 14:20-21)




ባሪያውም ፦ ጌታ ሆይ፣ እንዳዘዝኸኝ ተደርጎአል፣ ገናም ስፍራ አለ አለው። ጌታውም ባሪያውን ፦ ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤ እላችኋለሁና፣ ከታደሙቱ ከእነዚያ ሰዎች አንድ ስንኳ እራቴን አይቀምስም አለው። (ሉቃስ 14:22-24)




ሰዎች ያልመጡበት ሶስቱ ምክንያቶች ምንድን ነበሩ?

# My Property, My Stuff



ምክንያት #1

መሬት። በሌላ ቃላት፣ ንብረቴ


ጨርቃ ጨርቄ ካንተ ግብዣ የበለጠ ጠቃሚ ነው!




ምክንያት #2

የእኔ በሬዎች። በሌላ ቃላት፣ የእኔ ስራ (ስራዬ)

ስለ ግብዣህ እንዳላስብ፣ እኔ በስራ ዘርፌ በጣም ተወጥሬያለሁ!




ምክንያት #3

ሚስቴ! በሌላ ቃላት፣ ግንኙነቶቼ (ዝምድናዎቼ)

ሚስቴ፣ ቤተሰቤ እና ጓደኞቼ ከአንተ ግብዣ በላይ ጠቃሚ ናቸው!




ንብረቴ፣ ጨርቃ ጨርቄ ፣ሥራዬ፣ ግንኙነቶቼ:

በእነዚህ ምክንያቶች፣ ብዙ ሰዎች የኢየሱስን ታላቅ ግብዣ ያጣሉ (ከግብዣው ይቀራሉ)! የበጉን ሠርግ።




ለመነጠቅ ዝግጁ ለመሆን፣ በመጨረሻው ጊዜያት፣ በመንፈሳዊ መተኛት የለባችሁም። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው እውነት እላችኋለሁ፣ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።

(የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደጻፈው 24:45-47)




በኢየሱስ ላይ አተኩሩ! በመጨረሻው ጊዜያት አትዘናጉ! እናንተ እንዳትዘጋጁ ሊያደርጉ የሚችሉ ሺዎች ማዘናጊያዎች አሉ።




ወደ ፈተና አትውደቁ እና በመጨረሻ ጊዜያት ከኃጢአት ጋር አትስማሙ። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ። (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 26:41)





የሎጥን ሚስት አስታውሱ።

እሷ ሰዶምን እየለቀቀች ነበር። የሎጥ ሚስጥ በቃ ደርሳ (ለማምለጥ በጣም ቀርባ) ነበር፣ እሷ በጣም ደህና ሆና ነበር። ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜያት እሷ ወደ ሰዶም ዞረች።

እንደሷ አትሁኑ! ከጌታ መመለስ በፊት ባሉት ጊዜያት፣ ወደ ዓለም አትመለሱ!

(ኦሪት ዘፍጥረት 19:23-28)




በመጨረሻው የሩጫ ዙር ላይ አታቋርጡ!

በመጨረሻው ጊዜያት በጸሎት ቆዩ።

ኢየሱስ በሉቃስ 21 ውስጥ አስጠንቅቆናል፣ እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፣ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ። (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 21:36)





ጥሪያችሁን ችላ አትበሉ! ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ **ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም አለው።**

(የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምስራች) ሐዋርያው ቅዱስ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 9:62)




ኢየሱስ የታላቅ ፍቅር፣ ስሜት አምላክ ነው። እኛ የእርሱን ታላቅ ፍቅር፣ ስሜት ችላ ማለት ወይም መተው በፍፁም የለብንም። እርሱ በጣም በጥልቁ ስሜታዊ የሆነበት ምንድን ነው?




ኢየሱስ ነፍሳት ከሲኦል (ሲኦል ከመግባት) እንዲድኑ እጅግ በጣም ይፈልጋል! ለጠፋው ለእያንዳንዱ ነፍስ የእርሱ ልብ ይሰባበራል። እና እርሱ ሰዎችን ለማዳን የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ነው።




ይህን የእርሱን መሻት እኛ ችላ ካልን፣ እና ለጠፉት ወንጌልን መመስከር ካላስጨነቀን፣ ከዛ እኛ የእርሱን ጠንካራ ፍላጎት እየናቅን ነው!

የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት እያንዳንዱ ክርስቲያን የየራሳቸውን ድርሻ የግድ እየሰሩ መሆን አለባቸው።




የበጉ ሰርግ በመንግሥተ ሰማይ ምርጥ የምስጋናና የክብር የደስታ ጊዜ ግብዣ ይሆናል! ግን በመሬት(በምድር) የመጨረሻው መጥፎ ሰዓት(ጊዜ) ይሆናል።

ይህ የበጉ ሥርግ ማንም ክርስቲያን ሊያመልጠው የማይገባ የደስታ ጊዜ ግብዣ ነው።




ብዙ ሰዎች የጌታን የመመለሻ ቀን ገምተዋል። ነገር ግን ግምቶቹ እውነት ሆነው አልመጡም። መጽሐፉ ቀኑን ወይም ሰዓቱን ከእግዚአብሔር አብ በስተቀር ማንም እንደማያውቀው ግልጽ አድርጎታል። ብዙዎች የአሁን ነብያት ጌታን እርሱ ስለሚመለስበት ሰዓት ጠይቀውታል።

ነገር ግን እርሱ አንድም ቀን አልሰጣቸውም።





ኢየሱስ፣ ልክ በምሽት እንደሚመጣ ሌባ እርሱ ተመልሶ እንደሚመጣ ተናግሯል። ሰዎች ባልጠበቁት ሰዓት።

ከዮሐንስ ራእይ 16 ይህ ቃል እንዲህ ይናገራል... **እነሆ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።**




በአሁኑ ጊዜ፣ በዚህ ምድር ላይ ብዙ ክፉ እንዳይከሰት ጌታ ጥብቅ ቁጥጥር አድርጓል።

ኢየሱስ የእርሱን ሙሽራ ከወሰደ በኋላ፣ የጌታ የጥብቅ ቁጥጥር እጅ ይወጣል! (2ኛ ተሰሎንቄ 2:7)




ከ2ኛ ተሰሎንቄ ይህኛው ቃል፣ ይሄ እንዴት እንደሚሆን ያብራራል።

የዓመፅ ምስጢር አሁን ይሰራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። (2ኛ ተሰሎንቄ 2:7)




የክርስቶስ ሙሽራ ከሄዱ በኋላ፣ እና የጌታ የጥብቅ ቁጥጥር እጅ ከመንገዱ ከተነሳ ነኋላ፣ ዓለም በፍጥነት ጨለማ ውስጥ ይጠልቃል (ይገባል)!




የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ስለ የክርስቶስ ተቃዋሚ መነሳት እና ስለ አውሬው ምልክት 666 አስጠንቅቆናል።

ከመነጠቅ በኋላ፣ እግዚአብሔርን ለመከተል የበለጠ ከባድ ይሆናል።

ምክንያቱም በመከራው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን መከተል ህዝቦችን ሕይወታቸውን ያስከፍላቸዋል።

እኔ በግሌ የእስላም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከመነሳት ጀምሮ፣ እና ምልክቱ የነሱ (የእስላም የበላይ ‘ፕሮ ሙስሊም’ / የክርስቲያን ተቃዋሚ) የሃይማኖታቸው ሲስተም ሁሉም እንዲቀበል ያስገድዳሉ ብዬ አምናለሁ።




በዮሐንስ ራእይ 13-7 እንደሚለው፣ እሱ (አውሬው) ቅዱሳንንም ይዋጋቸው ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ሥልጣን ተሰጠው።


በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።




ብዙዎች የአውሬውን ምልክት 666 እንዲቀበሉ ይሰቃያሉ፣ እና ምልክቱን ስለተቃወሙ ብዙዎች ይገደላሉ። ግን የአውሬውን ምልክት 666 መቃወም አንድ ሰው እንዲድን ከሆነ (ለመዳን በሚያደርገው ጉዞ) በሙሉ ወሳኝነት አለው። ምክንያቱም ማንም የአውሬውን ምልክት 666 በእጃቸው ወይም በግምባራቸው ለተቀበለ ምንም ይቅርታ የለም፣ ምንም 2ኛ እድሎች የሉም። እነሱ ለአውሬው ናቸው፣ ለእግዚአብሔር ግን አይደሉም። እነሱ ወደ ሲኦል ይላካሉ። [ድህነት የሚገኘውም ኃጢአታችንን ተናዘን ንሰሃ ገብተን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርጎ በመቀበል በማመን፣ ኢየሱስም ስለኃጢአታችን በመስቀል ላይ እንደሞተና ከሙታንም እንደተነሳ በልባችን በማመንና በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ (አንድ ጌታ እግዚአብሔር) ስም በመጠመቅና እንደቃሉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አባት ፈቃድ ቅዱስ ሆኖ በመኖር ነው። የዮሐንስ ወንጌል 3:16 የዮሐንስ ወንጌል 10፣ የማቴዎስ ወንጌል 27-28፣ የዮሐንስ ወንጌል 6፣ የማርቆስ ወንጌል 16፣ የዮሐንስ ወንጌል 1፣ 1ኛ ዮሐንስ 1-5፣ የዮሐንስ ራእይ 21:8፣ የዮሐንስ ራእይ 13-22፣ ሮሜ 10:8-10፣ ኢየሱስ ጌታ ነው እግዚአብሔር ነው አዳኝ ነው፣ የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብ አምላክ ነው፣ የሠራዊት ጌታ የነገሥታት ንጉስ የጌቶች ጌታ የሰማይም የምድርም የሰውም የመላእክትም ለሚታየውም ለማይታየውም ፈጣሪ ነው። ኢየሱስ አለ በእኔ ያመነ የዘላለም ሕይወት አለው ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋገረ፣ በእኔ ያላመነ የዘላለም ሕይወት የለውም ኃጢአቱም አይሰረይለትም ተፈርዶበታል። ኢየሱስ ፍቅር ነው ሰላም ነው አምባ መጠጊያ ደግ እረኛ ቸር አምላክ አለት መታመኛ ረዳት ምርጥ እውነተኛ ወዳጅ፣ እውነት መንገድና ሕይወት ነው እርሱ እንደተናገረው። የእግዚአብሔር ልጅ ፈጣሪ ነው]





ታላቅ የክህደት ጊዜ ይሆናል!





በማቴዎስ መጽሐፍ እንደሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው፣ **ወንድምም ወንድሙን አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፣**

**ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ ይገድሉአቸውማል።** (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምሥራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 10:21)




እስከመጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።! በዚህ አስቸጋሪ ሰዓት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ መቆየት፣ ለአንድ ሰው ድህነት ወሳኝ ነው። (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምሥራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደፃፈው 24:13)




በመከራው ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ በምድር (በመሬት) ላይ ይፈሳል! (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ዮሐንስ ያሳየው ራእይ 15:7)




ዓለም ለፈፀማቸው ክፉ ሁሉ ተፈርዶበታል።


ይህ የተስፋፋ ጥፋት (ታላቅ ግራ መጋባት) እና ድንጋጤና ሀዘን ያደርጋል።

ብዙ ሕይወት ይጠፋል፣ እና ታላቅ ስቃይ ይሆናል።




How bad is it? Jesus said, unless those days were shortened, no one would survive.


ምን ያህል መጥፎ(ክፉ፣ጎጂ) ነው? ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ **እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤** (የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል (የምሥራች) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደጻፈው 24:22)




ዛሬ የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ችላ እያሉ ያሉት ብዙዎቹ ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በዚህ ምድር ላይ ሲመጣ እግዚአብሔርን ከሚረግሙት ጋር አንድ ናቸው (እነሱ ናቸው)።




አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከታላቁ መከራ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ተቋቁመው ይወጣሉ። ከዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ምዕራፍ 7 ማየት እንደምንችለው።





በዮሐንስ ራእይ 7:9-17 እንዲህ ይነበባል፣ ከዚህ በኋላ አየሁ፣ እነሆም፣ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ በታላቅም ድምፅ እንጮኹ:- በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ። መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ፊት በግምባራቸው ተደፉ፣ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ :- አሜን፣ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን አሜን አሉ። ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ :- እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ። እኔም :- ጌታ ሆይ፣ አንተ ታውቃለህ አልሁት።

አለኝም :- እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፣ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፣ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፣ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፣ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፣ ፀሐይም ትኩሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፣ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።




በታላቁ መከራ ውስጥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፀንተው በታማኝነት ላለፉት የተዘጋጁ ዙፋኖች አሉ። (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ዮሐንስ ያሳየው ራእይ 20:4)




ከዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20 እናንብብ፣ ዙፋኖችንም አየሁ፣ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፣ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን፣ ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ። (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ዮሐንስ ያሳየው ራእይ 20:4)




ይህ ሁሉ ምን ይላል፣

እኛ ምን ማድረግ ያስፈልገናል?




# ተዘጋጁ!!!

ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በነገሥታት ንጉስና በጌቶች ጌታ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ የተረጎመው፣ ቶማስ ጌታቸው ነው።

Translated to Amharic by Thomas Getachew Tuta, hithomasgetachew@gmail.com